# ኢትዮጵያና ኤርትራ ወደ ሠላም ወይስ ወደ ጦርነት?

የኢትዮጵያና የኤርትራ የድንበር ውዝግብ የመፍትሔ መሰናከል በሁለቱም ሀገሮች የዲሞክራሲያዊ መንግሥታት አለመኖር ነው ወደሚል መደመደሚያ ደርሷል።

*"የአንሚ አባላት ላከናወኑት ተግባር ኩራት ሊሰማቸው ይገባል ... የተባበሩት መንግሥታት ሠላም አስከባሪዎች (በኢትዮጵያና ኤርትራ መካከል ሠላም ለማስከበርና ለማስፈን) የሚቻላቸውን ሁሉ አድርገዋል። የተባበሩት መንግሥታት ጽ/ቤትም በኢትዮጵያና በኤርትራ መካከል ያለው ልዩነት (ግጭት) መፍትሔ እንዲያገኝ በማንኛውም ጊዜ ለመተባበር ዝግጁ ነው።" ይህ የአንሚ የህዝብ ግንኙነት ጽ/ቤት፣ ሐምሌ 23 ቀን 2000 ዓ.ም. የአንሚን ተልዕኮ መገባደድና ከኤርትራና ኢትዮጵያ ለቅቆ መውጣት አስመልክቶ በአስተላለፈው መግለጫ የጠቀሰው የአንሚ ልዩ ተወካይ ንግግር ነው።*

እንደሚታወቀው ሁሉ በግንቦት ወር 1990 ዓ.ም.፣ በኢትዮጵያና በኤርትራ መካከል ያልተጠበቀና ያልታሰበ፣ ድንበርን ምክንያት ያደረገ ግጭት ተከሰተ። ግጭቱ ባልተገመተ ፍጥነት ቅልጥ ወዳለ ጦርነት በማምራት፣ በ1991 እና በ1992 ዓ.ም. በተደረጉ በርካታ ውጊያዎች ከሁለቱም ወገን በድምሩ ወደ 70 ሺህ የሚጠጋ የሰው ሕይወት ሊጠፋ ችሏል። ጦርነቱ በሺህ የሚቆጠሩ ሰዎችን ከኤርትራ እና ከኢትዮጵያ የድንበር አካባቢ መኖሪያ ቀዬ አፈናቅሏል። በሁለቱ ሀገራት መሃከል የተደረገው ጦርነት፣ በሁለቱም ሀገራት ህዝቦች ላይ መጠነ ሰፊ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ቀውስ ፈጥሯል።

የኢትዮጵያና የኤርትራ መንግሥታት፣ ሁለት ዓመት በዘለቀ ጦርነት አቅማቸውን ከተፈታተሹ በኋላና በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ዜጐቻቸውን ሕይወት፣ በማይገባና እልባት ለሌለው ጦርነት ከማገዱ በኋላ፣ በሐምሌ 1992 ዓ.ም. በአፍሪካ አንድነት ድርጅትና በተባበሩት መንግሥታት አደራዳሪነት የአልጀርሱን ስምምነት (ውል) ተፈራረሙ። በዚህ ውል መሠረት የኢትዮጵያ መንግሥትም ሆነ የኤርትራ መንግሥት፣ የጀመሩትን ጦርነትና ግጭት ለማቆም፣ በይገባኛል ወደ ጦርነት የገቡበትን የመሬትና የድንበር ጉዳይ አጣርቶ፣ ድንበሩን የሚወስንና የሚያካልል ነፃና ወገንተኛ ያልሆነ የጋራ የድንበር ኮሚሽን ለማቋቋም፤ በዓለም አቀፉ ፍርድ ቤት (International Court of Justice) በሄግ የሚሠየመው የጋራ የድንበር ኮሚሽን፣ ሁለቱ መንግሥታት የሚያቀርቡት የይገባኛል ማስረጃ መርምሮ፣ የሚያሳልፈውን ውሳኔ ያለ ይግባኝ ለመቀበል እንዲሁም ደግሞ በሁለቱ ሀገራት ድንበር የተባበሩት መንግሥታት ሠላም አስከባሪ ጦር እንዲሠፍርና የድንበር ማካለሉ ተግባር እስኪፈጸም ድረስ እንዲቆይ ተስማሙ።

ይህንን ስምምነት መሠረት በማድረግ፣ የጋራ የድንበር ኮሚሽን ተቋቋመ። የተባበሩት መንግሥታት ሠላም አስከባሪ ጦር አንሚ (UNMEE) በሚል ስያሜና፣ በአልጀርሱ ስምምነት መሠረት በኤርትራ እና በኢትዮጵያ ድንበር መሃከል ሠፈረ። የጋራ ድንበር ኮሚሽኑ ሁለቱ መንግሥታት ያቀረቡትን የይገባኛል ማስረጃዎች መርምሬያለሁ ብሎ፣ የሁለቱን ሀገራት ወሰን (ድንበር) አስመልክቶ ውሳኔውን አሳወቀ፡ ውሳኔው በወቅቱ ሁለቱንም መንግሥታት እልል ያሰኘ ቢሆንም፣ ውሎ አድሮ ግን ከሁለቱም ወገን ቅሬታን አስነሳ። ቅሬታው በኢትዮጵያ ወገን ጠንከር ያለ ሆኖ በኤርትራ በኩል ደግሞ፣ የተወሰነው ተወስኗል፣ ውሳኔው ተግባራዊ ይሁን የሚል ምላሽ የተቸረው ነው። ሆኖም ግን በድንበር ኮሚሽኑ ውሳኔ ሁለቱ መንግሥታት ባለመስማማታቸው፣

ኮሚሽኑ ደከመኝ፣ ታከተኝ፣ አቃተኝ፣ ብሎ የሁለቱን ሀገራት ድንበር ምልክት በማስቀመጥ ሳያካልል (ዲማርኬት /Demarcate) ሳያደርግ፣ በኅዳር ወር 2000 ዓ.ም. ሥራውን አቁሞ ተበተነ። ከመበተኑ በፊት ግን በወረቀት የገለጽኩት ውሳኔ እንደ እውነተኛ ማካለል (Virtual demarcation) ይቆጠራል ብሎ አሳውቋል።

የተባበሩት መንግሥታት ሠላም አስከባሪ ኃይልም፣ ለስምንት ዓመታት በሁለቱ ሀገራት ድንበር አካባቢ ሠፍሮ ከቆየ በኋላ፣ የኤርትራ መንግሥት ባሳደረበት ከፍተኛ ጫና እና እክል፣ እንዲሁም ደግሞ ሁለቱም ሀገራት ወደተሻለ መቀራረብና ድርድር ባለማምራታቸው፣ የተልዕኮ ቀጠናውን ለቅቆ መውጣቱን አሳውቋል።

የድንበር ኮሚሽኑ ውሳኔ ተቀባይነት አለማግኘቱና የውሳኔው በማካለል ደረጃ ተግባራዊ አለመሆኑ የኮሚሽኑን ሥራ ውጤት አልባ አድርጐታል። የተባበሩት መንግሥታት ሠላም አስከባሪ ጦርም በ113 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ገደማ ዓመታዊ በጀት፣ ለስምንት ዓመታት ያህል በሁለቱ ሀገራት ድንበር ቢቆይም፣ ተልዕኮው ሳይሳካ ለመውጣት ተገድዷል። በኤርትራና ኢትዮጵያ መካከል ላለው የድንበር ውዝግብ፣ ዘላቂ መፍትሔ ለማስገኘት የተደረጉ ጥረቶች ውጤት አልባ ከመሆናቸው ጋር በተያያዘ፣ የሁለቱ ሀገራት መንግሥታት የወደፊት ግንኙነት ምን ሊሆን ይችላል? የሚለው ጥያቄ የአብዛኛው ኢትዮጵያውያንና ኤርትራውያን እንዲሁም የዓለም አቀፉ ኅብረተሰብ ጥያቄ ሆኗል። የወቅቱ ዐብይ ጥያቄዎች የድንበር ማካለሉ ተግባር አለመፈጸሙ፣ የድንበር ኮሚሽኑ ውሳኔ ተቀባይነት አለማግኘቱ፣ ይባስ ብሎ ደግሞ አንሚ የተልዕኮውን ቀጠና ለቅቆ መውጣት፣ በሁለቱ ሀገራት መንግሥታት ጦርነት ይቀሰቅሳል? የአንሚ እና የድንበር ኮሚሽኑ ፋይዳ ምን ነበረ? እና በኤርትራና ኢትዮጵያ መካከል ዘላቂ ሠላም ለማስፈን ያሉት የመፍትሔ አማራጮች ምንድን ናቸው? የሚሉት ናቸው።

## የድንበር ኮሚሽኑና የአንሚ ፋይዳ

በአልጀርሱ ስምምነት አንቀጽ አራት፣ ንዑስ አንቀጽ ሁለት መሠረት የተቋቋመው የድንበር ኮሚሽን፣ ያሣለፈው ውሳኔ የሁለቱን ሀገራት መንግሥታት የድንበር ውዝግብ ከመፍታት ይልቅ፣ ይበልጡን ያወሳሰበ ነበር። ለዚህ ዋና ምክንያቶች የሁለቱም ሀገሮች መንግሥታት ያቀረቧቸውን መረጃዎች፣ እራሱ በመሰለው መንገድ መተርጐሙ፣ የአልጀርሱ ስምምነት ድንበር መወሰኑና ማካለሉ፣ በ1900፣ በ1902 እና በ1908 ኢትዮጵያና ኢጣሊያ ባደረጓቸው የድንበር ውሎች መሠረት ይደረጋል ሲል፣ ኮሚሽኑ ግን ከእነዚህ ውሎች ውጭ የሆኑ መረጃዎችን መነሻና የውሳኔውም አንድ መሠረት ማድረጉ እና ውሳኔው ኤርትራንም ሆነ ኢትዮጵያን ለማስደሰትና ላለማስከፋት የተደረገ እንጂ፣ መረጃዎችን በመመርመርና በትክክል በመተርጐም ላይ የተመሠረተ አለመሆኑ ናቸው። ከዚህ በተጨማሪ ኮሚሽኑ የተልዕኮውን አንድ ክፍል (ድንበር መወሰንን- Delimitation) አማረም፣ አላማረም ከፈፀመ በኋላ፣ ዋናውን ተልዕኮ (ድንበር ማካለል- Demarcation) ሊያጠናቅቅ አልቻለም። ከመበተኑ አስቀድሞ ስለ ዋናው የማካለል ተልዕኮ አለመሳካት ሲገልጽም፣ የምችለውን አድርጌያለሁ ከዚህ በኋላ ሁለቱ መንግሥታት ቢፈልጉ ይደራደሩ፣ ባይፈልጉ ደግሞ ይዋጉ የሚል እንድምታ ያለው መልዕክት ነው ያስተላለፈው። የድንበር ኮሚሽኑ መቋቋም እና ውሳኔ ለሁለቱ ሀገሮች መንግሥታት የድንበር ውዝግብ የፈየደው ነገር የለም። ተልዕኮውን ሳያገባድድ መበተኑም፣ የኢትዮ-ኤርትራን የድንበር ውዝግብ አያባብሰውም? የድንበር ኮሚሽኑን ተልዕኮ አለመፈፀምና፣ አለመወጣት እንዲሁም መፍረስ አስመልክቶ፣ ታደሰ ገ/ወልድ የተባሉ ሰው (እኚህ ሰው በሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት ቁንጮ ናቸው እየተባለ በስፋት ይነገራል) "አዲስ ራዕይ" በተሰኘው የኢህአዴግ ልሣን በፃፉት ጽሑፍ "የኮሚሽኑ መፍረስ የተወሰነ ጥቅም ይሰጥ እንደሆነ እንጅ ጉዳት እንደሌለው መገንዘብ ይቻላል" ሲሉ አስፍረዋል። ታደሰ ጥቅም ይሰጣል ወዳሉት ጉዳይ በኋላ የምንመለስበት ሆኖ ኮሚሽኑ የፈጸመው ተግባር ግን እስከ አሁን በዓለም ከታዩ ድንበር የመወሰንና የማካለል ሥራዎች፣ እጅግ አሣፋሪ ሊባል የሚችል ነው።

የተባበሩት መንግሥታት ሠላም አስከባሪ ጦር፣ ለስምንት ዓመታት በሁለቱ ሀገሮች ድንበር ተወዝፎ ከቆየ በኋላ፣ ሁለቱ ሀገሮች በተለይም ኤርትራ በፈጸመችው ጫና የተልዕኮ ቀጠናውን ለቅቆ መውጣቱ፣ በአብዛኞች ግምት ሁለቱ ሀገሮች ወደ ዳግም ጦርነት እንዲያመሩ በር የከፈተና መንገዱን ያመቻቸ ነው። ይህንን አስመልክቶ ያነጋገርናቸውና በአንድ ወቅት ለጉዳዩ ቀረቤታ የነበራቸው፣ ነገር ግን ስማቸው እንዳይጠቀስ የፈለጉ ባለሥልጣን፤ የአንሚ በድንበሩ አካባቢ መስፈርና አሁን ደግሞ ለቅቆ መውጣት፣ ሁኔታዎችን እንደማይቀይር ይገልፃሉ። እኚህ ሰው እንደገለጹት አንሚ በሁለቱ ሀገሮች መንግሥታት መካከል ያለውን ጦርነት አላስቆመም። በሁለቱ መንግሥታት መካከል የነበረው ጦርነት የቆመው፣ የኢትዮጵያ መንግሥት በወሰደው አቋም ነው። የኢትዮጵያ መንግሥት በኤርትራ የድንበር ውዝግብ ሰበብ የተቃጣውን ጦርነትና ወረራ ከቀለበሰና ወሣኝ ድል ካስመዘገበ በኋላ፣ ዓላማዬና ግቤ ተሳክቷል ብሎ ጦርነት በማቆም፣ ውዝግቡን በሠላም ለመፍታት የአልጀርስን ስምምነት ፈረመ። በስምምነቱ መሠረት፣ የሁለቱ ሀገሮች መንግሥታት ጦርነት ካቆሙ በኋላ፣ አንሚ በስምምነቱ መሠረት በተፈጠረው የሠላምና ነፃ ቀጠና፣ ሁለቱ መንግሥታት ለስምምነቱ ተገዥና አክባሪ መሆናቸውን ለመቆጣጠር በቦታው ሠፈረ። አንሚ ከተሰጠው ተልዕኮ አኳያ የሁለቱ ሀገሮች መንግሥታት ወደ ጦርነት እንዳይገቡ፣ የመከልከል ሙብትና ሥልጣን አልነበረውም። ይህንን ላድርግ ቢል እንኳ ከነበረው ወታደራዊ ጥንካሬ አኳያ አቅሙ አይፈቅድለትም።

እንደ ባለሥልጣኑ ገለፃና አተያይ ከሆነ፣ አንሚ የተልዕኮ ቀጠናውን ለቅቆ ሊወጣ የቻለው፣ የኤርትራ መንግሥት ባሳደረበት ከልክ ያለፈና የአልጀርሱን ስምምነት የሚጥስና የሚቃረን ጫና ነው። የፕሬዝዳንት ኢሣያስና የመንግሥታቸው አቋም፣ መሬታችን በወራሪ ኃይል ተይዞ፣ አንሚ ደግሞ በወራሪ በተያዘው መሬታችንና በእኛ መሃከል መሰናክል ሆኖ ሲቀመጥ እጃችንን አጣጥፈን አንቀመጥም የሚል ነበር። ከዚህ በመነሳትም በአንሚ እንቅስቃሴ ላይ ከመጠን ያለፈ እክል በመፍጠር፣ ለመውጣቱ ዋነኛ ምክንያት ሆነዋል። አንሚ ወደ ድንበሩ አካባቢ የሠፈረው፣ ኤርትራና ኢትዮጵያ የአልጀርሱን ስምምነት ማክበራቸውን ለማየት እንጂ፣ ጦርነት ለማስቆም እስካልሆነ ድረስ የተልዕኮ ቀጠናውን ለቅቆ መውጣቱ፣ አዲስ ጦርነት እንደማይቀሰቅስ ባለሥልጣኑ ያመለክታሉ። ልክ እንደ ድንበር ኮሚሽኑ ሁሉ የአንሚ በድንበሩ አካባቢ መሥፈርና መውጣት ፋይዳ ቢስ ነው።

የአንሚንና የተባበሩት መንግሥታት ድርጅትን ሚና ፋይዳቢስ የሚያደርገው ሌላው ጉዳይ ደግሞ፣ የኤርትራ መንግሥት በአልጀርስ የፈረመውን ውል በመጣስ፣ የአንሚን ተልዕኮ በእጅጉ በሚያስተጓጉል ሁኔታ እንደፈለገ ሲፈነጭበት፣ ለረጅም ጊዜ ዝም ማለቱና እርምጃ አለመውሰዱ ነው። የጊዜያዊ የደህንነት ዞኑ (ቀጠና) (Temporary Security Zone) ከተመሠረተበትና የአንሚ ጦር በቀጠናው ከሠፈረበት ጊዜ አንስቶ፣ የኤርትራ መንግሥት በቀጠናው ሚሊሺያ ናቸው በሚል፣ መደበኛ ወታደሩን የወታደር የደንብ ልብሱን ብቻ ቀይሮ፣ ከነሙሉ ትጥቁ ሲያስገባ አንሚ አልከለከለውም። በተጨማሪም የኤርትራ መንግሥት በአንሚ እንቅስቃሴ የተለያዩ ገደቦች ሲጥል የተወሰደበት እርምጃ ወይም ሃይ ያለው ወገን አልነበረም። ሠላም ለማስከበር በመቶ ሚሊዮኖች ዶላር ተበጅቶለት የሠፈረ ኃይል፣ አንድ ሀገር በዓለም አቀፍ መድረክ የገባችውን ውል እየጣሰች ስታዋክበው ሰለቸኝ፣ በቃኝ ብሎ ተልዕኮውን የሚያቋርጥ ከሆነ፣ ጉዳዩ ከመጀመሪያው ፋይዳ ቢስ እንደሆነ ግልጽ ነው። ይህንን ፍሬ ቢስ ተግባር ነው የአንሚ ልዩ ተወካይ ቱኒዚያዊው አዞዘ አንፋር በጽሑፉ መግቢያ እንደጠቀሰው "አኩሪ ተግባር" ሲሉ ያሞካሹት።

## <u>በኤርትራና በኢትዮጵያ ዳግም ጦርነት ይቀሰቀሳል?</u>

አንሚ ተልዕኮውን አቋርጦ፣ ከኢትዮጵያና ኤርትራ ድንበር የደህንነት ቀጠና እንደሚወጣ ካሳወቀበት ቀን ጀምሮ፣ እስከአሁን አስተያየታቸውን በተለያዩ ሚዲያዎች የገለጹ ኢትዮጵያውያን፣ በሁለቱ ተቀናቃኝ መንግሥታት መካከል ዳግም ጦርነት እንደማይነሳ ግምታቸውን ሠንዝረዋል። ከዚህ በተቃራኒ ደግሞ እንደ ኢንተርናሽናል ክራይሰስ ግሩፕ (International Crisis

Group) ያሉት ዓለም አቀፍ ድርጅቶች፣ በኢትዮጵያና በኤርትራ መንግሥታት መካከል፣ ዳግም ጦርነት እንደሚቀሰቀስ ሥጋታቸውና ግምታቸው እንደሆነ እየገለጹ ይገኛሉ።

የኤርትራና የኢትዮጵያ መንግሥታት፣ በየፊናቸው በኦፊሴል በሚያወጧቸው መግለጫዎች፣ ጦርነት እንደማይፈልጉ አስታውቀዋል። የኤርትራ መንግሥት በዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት የተወሰኑልኝ ቦታዎች እስከተሰጡኝና ኢትዮጵያ እስካልወረረችኝ ድረስ፣ ጦርነት አልፈልግም ይላል። የኢትዮጵያ መንግሥትም በበኩሉ፣ ኤርትራ የኃይል አማራጭ እስካልመረጠች ድረስ፣ ጦርነት አልሻም ሲል በተደጋጋሚ አስታውቋል።

ቀደም ሲል በኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ወቅት ከፍተኛ ሥልጣንና ወሣኝ ሚና የነበራቸው ሰው እንደሰጡን አስተያየት ከሆነ፣ ከአልጀርሱ ስምምነት በኋላ ኢትዮጵያና መንግሥቷ ለሠላም ተገዥ ቢሆኑም፣ ኤርትራ ግን የጀመረችውን ጦርነት በአዲስ መልክና በአዲስ ግንባር ቀጥላለች። የኤርትራ መንግሥት የጦርነት ስትራቴጂውን ከመደበኛና ቀጥተኛ ጦርነት በመቀየር፣ የኢትዮጵያ መንግሥት ተቀናቃኝ የሆኑ የሶማሊያ እስልምና አክራሪዎችንና አሸባሪዎችን፣ በተጨማሪም በትጥቅ ትግል የኢትዮጵያን መንግሥት የመጣል ዓላማ ያላቸውን እንደ ኦነግ፣ ኦብነግና አርበኞች ግንባር ያሉ የፖለቲካ ድርጅቶችን የትጥቅና የሥልጠና ድጋፍ በመስጠት፣ የኢትዮጵያን መንግሥት በመፈታተን ላይ ይገኛል። ፕሬዝዳንት ኢሣያስና መንግሥታቸው፣ በኦፊሴል በሚሰጧቸው መግለጫዎች፣ ጦርነት እንደማይፈልጉ ይፋ ቢያደርጉም፣ በተግባር ግን በሕግ የተፈረደልኝን መሬትና ዳር ድንበር በኃይልም ቢሆን እወስዳለሁ የሚል ዛቻ ያለው መልዕክት በተደጋጋሚ እያስተላለፉ ነው። በመሆኑም ኤርትራ ሥራዋን እየሠራች ነው ይላሉ ባለሥልጣኑ።

ባለሥልጣኑ የኢትዮጵያን መንግሥት ሁኔታ እንደሚከተለው ያስቀምጡታል፤ የኢትዮጵያ መንግሥት እስከ አሁን ድረስ የተያያዘው የቃላት ጦርነት ነው። በሶማሊያና በምሥራቅ ኢትዮጵያ ከኤርትራ ጋር የውክልና ጦርነት (Proxy-War) ላይ ቢሆንም፣ የኤርትራን መንግሥት ተቃዋሚ ኃይሎችን በማስታጠቅና በማደራጀት፣ ለማዳከም ያደረገው ሙከራ የለም። በቅርቡ የኤርትራ ተቃዋሚ ኃይሎችን በአዲስ አበባ እንዲሰባሰቡ ቢፈቅድም፣ መድረኩን ከመፍጠር ባለፈ ያደረገው አንዳችም ነገር የለም። በቃላት ደረጃ ግን የኤርትራ መንግሥት ጦርነት ከጫረ፣ ድንበርና ሉዓላዊነትን ከማስከበር አልፎ ተርፎ፣ የኢሣያስን መንግሥት ሊገረስሰው እንደሚችል የሚያመላክቱ ንግግሮችን በተደጋጋሚ አሰምቷል።

ከእነዚህ ነባራዊ ሁኔታዎች በመነሣት፣ በሁለቱ ሀገሮች መንግሥታት መካከል፣ የጦርነት በድጋሚ መቀስቀስ ሊከሰት የሚችል ጉዳይ እንደሆነ ይገልፃሉ። ጦርነት ሊቀሰቀስ የሚችለውም በሁለቱም መንግሥታት መሪዎችና ወሣኝ ባለሥልጣናት በሚደረጉ የተሳሳቱ ስሌቶች እንደሚሆን ባለሥልጣኑ ይገልፃሉ። እነዚህ ስሌቶች የሚመነጩት፣ ከሁለቱም መንግሥታት ወገን ያሉት መሪዎች፣ መካሮቻቸውና አጋሮቻቸው፣ ስለሌላው መንግሥትና መሪ በሚያደርጉት ግምገማና የይሆናል ግምቶች ነው፤ የጦርነቱ መንስዔ የሚሆኑት ስሌቶች የሚከተሉት ሊሆኑ ይችላሉ።

1ኛ. የኤርትራ መንግሥት፣ የኢትዮጵያ መንግሥት በተደራራቢ ችግር ኢኮኖሚው ተዳክሟል፣ ወታደራዊ ኃይሉ አስተማማኝና ጠንካራ አይደለም፣ ህዝቡ መንግሥትን አይደግፈውም (አይፈልገውም)፣ ከግራ ቀኙ የታጠቁና ያልታጠቁ ተቃዋሚ የፖለቲካ ኃይሎች እያዋከቡት ነው ብሎ ካሰበ፣ ጦርነት ሊጀምር ይችላል። በተመሳሳይ መልኩ የኢትዮጵያ መንግሥትም የኤርትራ መንግሥት ወታደራዊ ኃይሉ የተመናመነ ነው፣ የሠራዊቱ የትጥቅና የሎጂስቲክስ ድርጅት አነስተኛ ነው፣ መንግሥቱ ህዝባዊ መሠረትና ድጋፍ የለውም ብሎ ካሰበና ካመነ ጦርነት ሊጀምር ይችላል።

2ኛ. የሁለቱም ሀገሮች መንግሥታት፣ ጦርነቱ የፖለቲካ ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ ምቹ ሁኔታ የሚፈጥር ከሆነ፣ ጦርነት ሊቀሰቅሱ ይችሉ ይሆናል። እንደሚታወቀው ሁለቱም መንግሥታት ለህዝባቸው ቃል የገቡትንና ቀን ተሌት የሚለፍፉትን፣

ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ተግዳሮት ማሟላት ተስኗቸዋል። ሁለቱም መንግሥታት በሀገር ውስጥም ሆነ በዓለም አቀፉ ኅብረተሰብ፣ ስለ ኢፍትሃዊነታቸው፣ የዴሞክራሲ ሥርዓት ስላለማስፈናቸው፣ ሰብዓዊ መብት ስለመጣሳቸው እና የህዝባቸው ድህነት መንስዔ ስለመሆናቸው፣ ከባድ ወቀሣ እየቀረበባቸው ነው። በሀገራቸው ውስጥ ያለው የህዝብ እሮሮና ጥያቄም፣ ከዕለት ወደ ዕለት እየጠነከረና ሞጋች እየሆነ መጥቷል። እንዲህ ባለው ሁኔታ ከሀገር ውስጥም ሆነ ከዓለም አቀፉ ኅብረተሰብ የሚሠነዘረውን ወቀሣና ጥያቄ ለማምለጥና ትኩረቱንም ለማስቀየስ፣ አንዳቸው ጦርነት ሊጀምሩ ይችላሉ። ባለሥልጣኑ እንደሚሉት ከሆነ እንዲህ ዓይነቱን ስሌት ኢትዮጵያ በ1998 ዓ.ም. በሶማሊያ ተጠቅማበታለች።

3ኛ. የኤርትራ መንግሥት በሶማሊያ የሚገኙ ፀረ-ኢትዮጵያ እና ፀረ-ኢህአዲግ ኃይሎች በማስታጠቅ የኢትዮጵያን ሕልውና እና ሉዓላዊነት ብትፃረርም እንዲሁም ደግሞ የሶማሊያ እስላማዊ ፍርድ ቤቶች ሕብረት በኢትዮጵያ ቢዝትና ኦጋዴንን የመገንጠል ዓላማ እንዳለው ቢያሣውቅም፣ በወቅቱ እንደ ከፍተኛና ፈታኝ አደጋ ሊቆጠር የሚችል አልነበረም። የኢትዮጵያ መንግሥት የኤርትራን እጅ አዙር ትንኮሣ እና የእስላማዊ ፍርድ ቤቶችን ሕብረት ዛቻ ምክንያት አድርጐ፣ በአደገኛ ሁኔታ ተደራጅተውና አቅም ገንብተው ሊያጠፉኝ ነው ወዳላቸው የሶማሌ ኃይሎች ዘመተ። አደገኛና እጅግ የተደራጀ የተባለው የሶማሌ እስላማዊ ፍርድ ቤቶች ሕብረት ኃይልም፣ በሁለት ቀን ጦርነት ተንኮታኮተ። የኢትዮጵያ መንግሥት ዋና ዓላማ የሶማሊያን ኃይሎች መደምሰስ ሳይሆን፣ ምርጫ 97 ያስከተለውን የሀገር ውስጥና ከሀገር ውጭ እሮሮና ነቀፌታ፣ የትኩረት አቅጣጫ ማሣት ነበር። ከሀገር ውጭ ያለውን በተለይም የአብዛኛውን የዓለም አቀፍ ኅብረተሰብና ድርጅቶች ትኩረት፣ በትክክል ወደ ሶማሊያ እንዲዞር አድርጓል። በሀገር ውስጥ ያለውን የፖለቲካ ትኩረት ግን ወደ ሶማሊያ እንዲያተኩር ለማድረግ አልቻለም።

የኢሣያስ መንግሥትም በኤርትራ ምድር፣ ከነፃነት በኋላ የተፈጠረውን የኢኮኖሚ ድቀት፣ ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ምስቅልቅል፣ አፈና እና ጭቆና፣ የኤርትራ ህዝብና ዓለም አቀፉ ኅብረተሰብ እንዳያተኩርበት የሚጠቀምበት ዘዴ፣ ኢትዮጵያን ምንጊዜም እንደ ወራሪ እና የኤርትራ ነፃነት ጠላት አድርጐ መፈረጅ ነው። የኢሣያስ ዓይነተኛ ተግባር የኤርትራ ህዝብ ከግል ኑሮው ይልቅ፣ ስለኢትዮጵያ ወራሪነትና ጠብ አጫሪነት እንዲያስብ ማድረግ ነው። በአጠቃላይ የኤርትራም ሆነ የኢትዮጵያ መንግሥት፣ የፖለቲካ ዓላማቸውን የሚያሳሣካላቸው እስከሆነ ድረስ ጦርነት ሊቀሰቅሱ ይችላሉ። ጦርነት ባይኖርም እንኳ ኤርትራ ልትወረኝ ነው፣ ኢትዮጵያ ልትወረኝ ነው በሚል ሰበብ የጦርነት ደመና ያንዣበበ ማስመሰሉ፣ አንፃራዊ የፖለቲካ ጥቅም እንደሚሠጣቸው ግልጽ ነው።

4ኛ. የሁለቱ መንግሥታት መሪዎች በፍጹም አይተማመኑም፤ አንዱ ለሌላው ያላቸው አመለካከት ያጠፋኛል የሚል ነው። ከዚህም የተነሣ ከግጭቱ ጊዜ አንስቶ እስከ አሁን፣ በሁለቱ ሀገራት መሪዎችና ባለሥልጣናት መካከል፣ ኢምንት እንኳ የመረጃ ልውውጥ ወይም የሚገናኙበት የጋራ መድረክ የለም። መሪዎቹና መንግሥታቱ እርስ በእርስ ካለመተማመናቸው የተነሳ፣ በድንበሩ አካባቢ በቅርብ ርቀት ወታደሮቻቸውን በተጠንቀቅ አስፍረዋል። እንዲህ ባለው ሁኔታ የአጋጣሚ ግጭት ወይም ድንገተኛ የተኩስ ድምፅ እንኳ ቢሰማ፣ ሁለቱም ወገኖች አንዱ ሌላውን ሊያጠፋኝ ጦርነት መጀመሩ ነው በሚል ስጋት፣ ቅልጥ ወዳለ ጦርነት ሊገቡ ይችላሉ። ከዚህ በተጨማሪ የሁለቱም ሀገር መንግሥታት መሪዎች፣ አምባገነንና ተመሳሳይ ባህሪ ያላቸው ናቸው። የሀገሮቻቸውም ችግር ከሞላ ጐደል ተመሳሳይ ነው፤ ይህ ደግሞ የጦርነት ሥጋቱንና የመቀስቀስ ዕድሉን ከፍ ያደርገዋል። ከሁለት አንዱ እንኳ የተለየ ባህሪና አመለካከት ቢኖራቸው፣ ነገሮችን ወደ ትክክለኛ መስመር የማስገባትና የጦርነትን ሥጋት የመቀነስ አዝማሚያና ዕድል ሊኖር ይችል ነበር።

## ጦርነት የመቀስቀሱ ዕድል ሰፊ ነው

ከላይ በዝርዝር የሠፈሩት የባለሥልጣኑ ትንበያዎች እንደተጠበቁ ሁነው፣ በቅርብ ዓመታት የታየው የሦስተኛ ወገኖች ሠላም የማስፈንና ሁለቱን ወገኖች የማቀራረብ ጥረትና ሂደት፣ እየመነመነ መጥቶ አሁን ያለበት ደረጃ መድረሱና፣ ከቅርብ ወራት ወዲህ ደግሞ በድንበር አካባቢ በሁለቱም መንግሥታት የሚደረጉ ወታደራዊ እንቅስቃሴዎች፣ በሁለቱ መንግሥታት መካከል ጦርነት የመቀስቀሱ ዕድል ሰፊ መሆኑን የማያመላክቱ ናቸው።

ከድንበር ውዝግቡና ጦርነቱ መጀመር ጊዜ አንስቶ፣ ሁለቱ መንግሥታት ልዩነታቸውን በድርድርና በሠላም እንዲፈቱ ሽር ጉድ ሲሉ የነበሩት፣ እንደ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት (አፍሪካ ሕብረት)፣ የተባበሩት መንግሥታት፣ አሜሪካ እና ሩዋንዳ ያሉት ሦስተኛ ወገኖች ጥረታቸውን ሙሉ በሙሉ አቁመዋል። ሁሉም ጦርነት እንዳትጀምሩ እናሳስባለን ከማለት ያለፈ ያሳዩት ተቆርቋሪነትና የፈጸሙት የሽምግልና ተግባር የለም። ከአልጀርሱ ስምምነት ማግሥት ጀምሮ ሁለቱም መንግሥታት የጦር መሣሪያ በመሸመት፣ ሠራዊታቸውን በማሠልጠንና በማደራጀት የጦር ኃይላቸውን እያጠናከሩ ነው። አንደኛው መንግሥት ለሌላው ያለው አመለካከትም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየሻከረ መጣ እንጂ አልተሻሻለም።

በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ ሠራዊት የድንበር ግጭቱ ከመጀመሩ (ግንቦት 6/1990) አስቀድሞ፣ በኢትዮጵያ ይዞታ ስር የነበረውን መሬት በመያዝ፣ ይህንን ይዞታና ድንበር ለመንጠቅ ወይም ለመጣስ የሚደረግ እንቅስቃሴን፣ ሉዓላዊነትን እንደመድፈር በመቁጠር ምላሽ ለመስጠት የተዘጋጀ ነው። የኤርትራ ሠራዊት የደህንነት ቀጠናውን ሙሉ በሙሉ የያዘ ቢሆንም፣ ዋና ጥያቄውና እንቅስቃሴው ሊሆን የሚችለው በባድመ፣ ጾረና እና ኢሮብ አካባቢ በኢትዮጵያ ሠራዊት ስር ያሉ፣ ነገር ግን የድንበር ኮሚሽኑ ውሳኔ፣ ለኤርትራ ይገባሉ ያላቸውን ቦታዎች በቁጥጥሩ ስር ማድረግ እንደሆነ ግልጽ ነው። እንዲህ ዓይነቱ ፍጥጫ ካለፈው የድንበር ግጭትና ጦርነትም እጅግ የባሰ ነው። ምንም እንኳ የድንበር ግጭቱ በግንቦት 1990 ዓ.ም. ጀምሮ በአጭር ጊዜ ወደ አጠቃላይ ጦርነት ቢያመራም፣ ያኔ የነበረው አንድ አማራጭ በሦስተኛ ወገን መዳኘት ነው። በአሁኑ ፍጥጫ ግን "በሕግ አምላክ!" የሚልና የዳኝነትን አማራጭ ግምት ውስጥ የሚያስገባ ሳይሆን እወስዳለሁ፣ አትወስድም ነው። ጦርነቱም ከተጀመረ ካለፈው የባሰና ረጅም ጊዜ የሚፈጅ ሊሆን ይችላል።

ጦርነት ከተቀሰቀሰ የኤርትራ ስትራቴጂ ሊሆን የሚችለው፣ በድንበሩ አካባቢ የመከላከል ጦርነት እያደረጉ፣ በሱማሌ በኩል የኢትዮጵያን መንግሥት የሚቃወሙ ኃይሎችን በትጥቅና በሰው ኃይል እያጠናከረ፣ ኢትዮጵያን በሁለት ግንባር ጦርነት መወጠር ነው። ከዚህ በተጨማሪ ኤርትራ ካለፈው በመማር፣ አየር ኃይሏን ለማጠናከር ደፋ ቀና ስትል ከርማለች። ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር የምታደርገውን ጦርነት የሚያግዙ፣ የውጪ ኃይሎች እንዳሉም ግልጽ ነው። እነዚህ ሁሉ ታሳቢ ከተደረጉ፣ የኢትዮጵያ ወታደራዊ ኃይል የቱንም ያህል የተጠናከረ ቢሆን እንኳ፣ ኤርትራን በቀላሉ ድል ማድረግ የሚቻል አይመስልም።

## No Peace No War

ታዋቂውን የታሪክ ፕሮፌሠር ተክስተ ነጋሽን ጨምሮ፣ የኤርትራና የኢትዮጵያ መንግሥታት ወደ ዳግም ጦርነት አይገቡም፣ የሚሉ ሰዎች ያላቸው አመለካከት በሁለቱ መንግሥታት "ሠላምም ጦርነትም አይኖርም" (No Peace No War) የሚል ነው። ይህን ሃሳብና ግምት የሚሰነዝሩ ሰዎች የግምታቸው /ሃሳባቸው/ መነሻ ነጥቦች ሁለት ናቸው። የመጀመሪያው ነጥብ በሁለቱ ሀገሮች መካከል ሠላም ያመጣሉ ተብለው፣ ተስፋ ተጥሎባቸው የነበሩት የድንበር ኮሚሽኑ ውሳኔና፣ የተባበሩት መንግሥታት ሠላም አስከባሪ ኃይል ጥረት (ምንም እንኳ ጥረታቸው አመርቂ ባይሆንም) መና ሆኖ መቅረት ነው። ሁለተኛው

ነጥብ ደግሞ፣ ሁለቱም መንግሥታት የውስጥ የፖለቲካ ምስቅልቅል ያለባቸውና፣ ኢኮኖሚያቸውም እየቆረቆዘ የሚሄድ መሆኑን መሠረት በማድረግ፣ ሁለቱም መንግሥታት ጦርነት የሚያስከትለውን ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊና አኮኖሚያዊ ቀውስ በመፍራት፣ ከትንኮሳና ጦርነት ከመቀስቀስ ይታቀባሉ የሚል አስተሳሰብ ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ የኢትዮጵያም ሆነ የኤርትራ መንግሥት ገዢ ፖርቲዎች፣ ከ1983 ዓ.ም. ከነበራቸው ግንኙነት አኳያ ሲታይ፣ አንዱ የሌላውን ሕልውና ለማጥፋት አቅሙና ሁኔታው እንኳ ቢፈቀድላቸው፣ አይከጅሉትም የሚል አስተያየት የሚሰነዝሩ ወገኖች አሉ። ይህን ሃሳብና አመለካከት የሚያራምዱ ሰዎች ፍሬ ነገር፣ የኤርትራ መንግሥት ዋና ፍላጎት የኢህአዲግን መንግሥት የተፍረከረከና ደካማ ማድረግ እንጂ፣ ጨርሶ ማጥፋትና በሌላ መተካት አይደለም ይላሉ። በተመሳሳይ መልኩ የኢትዮጵያ መንግሥት ፍላጐትም፣ የኢሣያስና የህዝባዊ ግንባር ሓርነት ኤርትራን መደምሰስ ሳይሆን፣ ማዳከምና ስጋት እንዳይሆነው ማድረግ ነው። ህዝባዊ ግንባርና ኢሣያስ፣ እንደ ኢህዲግና መለስ ተለሳልሶ የሚይዛቸው መንግሥት አያገኙም፤ ኢህዲግና መለስም ኢሣያስ ምንም ያክል ቢደነፉ፣ ሊደመስሳቸው ልቡ እንደማይጨክን ይተማመናሉ። ስለዚህ በሁለቱ መንግሥታት መካከል ሠላምም ጦርነትም ሳይኖር ጊዜ ይዘልቃል።

"No Peace No War" የሚለው ግምትና ትምበያ ሊሠራ የማይችልበት አንድ ትልቅ ጉዳይ አለ፤ ይኸውም የኤርትራ መንግሥት ሕልውና እና ህዝባዊ ድጋፍ እንዲሁም የኤርትራ ህዝብ የአንድነት ስሜት መሠረታዊ ጉዳይ ናቸው። የኤርትራ መንግሥት ሕልውና እና ህዝባዊ ድጋፍ የሚመነጨውና የተመሠረተው፣ በኢትዮጵያ ላይ ካለው ጥላቻና የወራሪነት አመለካከት፣ ብሎም ኢትዮጵያ የኤርትራ ሕልውና እና ሉዓላዊነት ዋና አደጋ ናት በሚሉ የተሳሳቱ አመለካከቶች ነው። እንዲህ ዓይነቶችን አመለካከቶች የኤርትራ መንግሥት ከነፃነት ማግስት ጀምሮ በህዝቡ ዘንድ እንዲሰርጽ አድርጓል፣ እያደረገም ነው። ብዙም ባይሆኑ በኤርትራ በኃይማኖት፣ በቋንቋ እና በባህል የተለያዩ ህዝቦች (ብሔሮች) አሉ። የዲሞክራሲ፣ የመብት፣ የፍትህና የእኩልነት ጉዳይ ከተነሳ፣ አሁን ካለው ነባራዊ የፖለቲካ ሁኔታ ሲታይ፣ ህዝቦቹ (ብሔሮቹ) ይከፋፈሉና የኤርትራ የፖለቲካ አንድነትና ሕልውና ያከትምለታል። በኤርትራ ያሉ ብሔሮችን አንድ ያደረጋቸው፣ ለዘመናት የቆየ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ባህላዊ ትስስር ሳይሆን ለኢትዮጵያ ያላቸው ኃይለኛ ጥላቻና የአደጋ አመለካከት ነው።

የኢሣያስ መንግሥት ይህንን አመለካከት፣ በቃላት ፕሮፖጋንዳ ብቻ ለዘመናት እንዲኖር ሊያደርገው አይችልም። ጥላቻውና አመለካከቱ የበለጠ እንዲሰርጽና የእውነት ገጽታ እንዲላበስ ለማድረግ፣ ተሸነፈም አልተሸነፈም፣ ከሰረም አተረፈም፣ ከኢትዮጵያ ጋር ጦርነት መግጠም ግድ ይለዋል። በኤርትራ መንግሥት በኩል የጦርነት ትንኮሣው ከመጣ፣ የኢትዮጵያ መንግሥት አፀፋ በጠቅላይ ሚኒስትር መለስ እንደተገለጸው "የማያዳግም እና የመጨረሻ ነው" የተባለ ቢሆንም አሁን ላይ ሆኖ እርግጠኛ መሆን ያስቸግራል።

## ኢትዮጵያና ኤርትራ ጤናማ ግንኙነት ሊጀምሩ ይችላሉ?

የኢትዮጵያና የኤርትራን የድንበር ውዝግብና ግጭት፣ ዘላቂ መፍትሔ አስመልክቶ፣ በተለየዩ ጊዜያት ከነበሩ ሁኔታዎች በመነሣት የተለያዩ ሃሳቦች ተሠንዝረዋል። በአልጀርሱ ስምምነት ማግስት፣ በብዛት ይንፀባረቅና ይሰነዘር የነበረው ሃሳብ፣ ሁለቱም ወገኖች (መንግሥታት) ያለ ይግባኝ እንቀበለዋለን ሲሉ የተስማሙበትን የድንበር ኮሚሽኑ ውሳኔ፣ መቀበልና መተባበር ነበር። የድንበር ኮሚሽኑ ውሳኔውን ይፋ ሲያደርግ፣ ሁለቱም መንግሥታት በየበኩላቸው ውሳኔው አርክቶናል፣ አሸናፊ አድርጎናል ብለው የአፊሴል መግለጫ ሲሰጡ፤ ይህ የመፍትሔ ሃሳብ ለመሳካት የተቃረበ መስሎ ነበር። ሆኖም ግን የኢትዮጵያ መንግሥት ውሎ፣

አድሮ ውሳኔው ችግር አለበት፣ ችግር ቢኖርበትም ግን በመሠረተ ሃሳብ ደረጃ፣ ከነስህተቱ ተቀብሎ የድንበር ማካለሉ ሂደት ላይ ስህተቱ እንዲስተካከል እፈለጋለሁ ሲል መፍትሔነቱ አበቃለት። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ በሦስተኛ ወገን ውሳኔ አደራዳሪነት የሚደረግ መፍትሔ ቦታ እያጣ መጣ።

የኤርትራ መንግሥት እንደ ብቸኛ መፍትሔ የሚቆጥረው፣ የድንበር ኮሚሽኑ በወረቀት ላይ ባሠፈረው ውሳኔ መሠረት፣ ለኤርትራ ይገባሉ የተባሉት ቦታዎች ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ ለኤርትራ ሲሰጡ ብቻ ነው የሚል ነው። በዚህ አቋምና መፍትሔ መደራደርና መነጋገር እንደማያስፈልግም ገልጿል። የኢትዮጵያ መንግሥትን የመፍትሔ ሃሳብ፣ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ በብዙ አጋጣሚዎች አስታውቀውታል። ታደሰ ገ/ወልድም "በአዲስ ራዕይ" መጽሔት "ከድንበር ውዝግቡና ከድንበር ኮሚሽኑ ባሻገር" በሚል ጽሑፍ አስፍረውታል። (ከአፃፃፍ ዘይቤውና ከቃላት አጠቃቀሙ በመነሣት የአዲስ ራዕዩ ታደሰ ገ/ወልድ፣ ጠቅላይ ሚኒስቴር መለስ ዜናዊ ናቸው የሚል ግምት አለን)። የኢትዮጵያ መንግሥት መፍትሔ ሁለት ናቸው፤ አንደኛውና የአጭር ጊዜ መፍትሔው፣ ሁለቱም መንግሥታት የድንበር ኮሚሽኑን ውሳኔ፣ በመሠረተ ሃሳብ ደረጃ ተቀብለው፣ በድንበር ማካለሉ ሂደት ማሻሻያዎች በማድረግ፣ ድንበሩን መከለልና ውዝግቡን መፍታት ነው። ሁለተኛውና የረጅም ጊዜ መፍትሔው ከድንበር ውዝግቡም ባለፈ ሁኔታ በሁለቱ ሀገሮችና መንግሥታት መካከል ጤናማ ግንኙነት መመሥረት ነው።

የኤርትራ መንግሥት የመፍትሔ ሃሳብና፣ የኢትዮጵያ መንግሥት የአጭር ጊዜ መፍትሔ ሃሳብ፣ አሁን ዋጋ የሌላቸው ናቸው። ምክንያቱም ድንበር ኮሚሽኑ የማካለል ሥራውን ንክች ሳያደርግ፣ ሁለቱንም ሀገሮች የራሳችሁ ጉዳይ ብሎ ተበትኗል።

እንደ ታደሰ ገ/ወልድ ትንተና ከሆነ፣ ይህ ለኢትዮጵያ መንግሥት ጥሩ አጋጣሚ ነው፤ ጥሩ አጋጣሚ የሚሆንበትም ምክንያት፣ የድንበር ኮሚሽኑ ሳይፈርስ ኤርትራ ለድርድር፣ አሻፈረኝ ብላ ስለነበር እና አሁን ኮሚሽኑ በመፍረሱ፣ ኤርትራ ስትለመን አሻፈረኝ ያለችውን ድርድር በግድም ሆነ በውድ ትቀበላለች የሚል ነው። የኤርትራ ድርድርን የመቀበልና ያለመቀበል ጉዳይ ራሱን የቻለ ሆኖ፣ ዋናው ጥያቄ ኢትዮጵያና ኤርትራ ጤናማ ግንኙነት (normal relationship-normalization) ሊመሰርቱ ይቻላቸዋል? የሚለው ነው።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እና በተለይ አሁን፣ በርካታ ወገኖች ለኢትዮጵያና ለኤርትራ ችግር ዘላቂ መፍትሔ፣ ብሎም ደግሞ ለአፍሪካ ቀንድ ሀገሮችና አካባቢ የፖለቲካ ቀውስ መብረድና መረጋጋት ዘላቂው መፍትሔ የኢትዮጵያና የኤርትራ ጤናማ ግንኙነት መመሥረት ነው ብለው ያምናሉ። ይህ በእርግጥ ትክክል ነው፤ ግን በሁለቱ ሀገሮች ያለው የፖለቲካ ሁኔታ መንግሥታቱን ጤናማ ግንኙነት ለመመሥረት ፈቃደኛና ዝግጁ እንዲሆኑ የሚያስችልና የሚጋብዝ አይደለም። የሁለቱ ሀገሮች ውዝግብ በአመዛኙ፣ የሁለት ሀገሮች ህዝብ ችግር ሳይሆን የሁለቱ አምባገነን መንግሥታት ችግር ነው። ሁለቱም መንግሥታት ለህዝባቸው ምርጫና ፍላጎት ቦታ የማይሰጡ ከመሆን ባሻገር፣ እኔ እበልጥ፣ እኔ እበልጥ የሚፎካከሩ ናቸው። ስለዚህም ነው ኢህአዲግና መለስ፣ ህዝባዊ ግንባር ሓርነት ኤርትራና ኢሣያስ፣ በሥልጣን እስካሉ ድረስ፣ ኢትዮጵያና ኤርትራ እንኳንስ ጤናማ ግንኙነት ሊመሠርቱ ይቅርና የድንበር ውዝግቡንም ሊፈቱ አይችሉም።